የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ—ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No.1
ADDIS ABABA-14th October, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፩/፲፱፻፺፮
ዓለም አቀፍ ጠቀሜታ ያላቸው ተንቀሳቃሽ ዕቃዎች ኮንቬንሽንና የአውሮፕላን ዕቃዎች ፕሮቶኮል ማጽደቂያ
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፪ሺ፬፻፭

## CONTENTS

Proclamation No. 371/2003
The Convention on International Interests in Mobile Equipment and the Protocol to the Convention on Matters specific to Aircraft Equipment Ratification Proclamation ........................................... Page 2405

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፩/፲፱፻፺፮
### ዓለም አቀፍ ጠቀሜታ ያላቸው ተንቀሳቃሽ ዕቃዎች ኮንቬንሽንና የአውሮፕላን ዕቃዎች ፕሮቶኮልን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ዓለም አቀፍ ጠቀሜታ ያላቸው ተንቀሳቃሽ ዕቃዎች ኮንቬንሽንና የአውሮፕላን ዕቃዎች ፕሮቶኮል እ·ኤ·አ· ኖቬምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ በደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን ከተማ የተፈረመ በመሆኑ።

ኮንቬንሽኑና ፕሮቶኮሉን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቃቸው ስለሆነ፣

በሕገ – መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ዓለም አቀፍ ጠቀሜታ ያላቸው ተንቀሳቃሽ ዕቃዎች ኮንቬንሽንና የአውሮፕላን ዕቃዎች ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፩/፲፱፻፺፮ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ኮንቬንሽኑና ፕሮቶኮሉ ስለመጽደቃቸው

እ·ኤ·አ ኖቬምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ በደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን ላይ የተፈረሙት የዓለም አቀፍ ጠቀሜታ ያላቸው ተንቀሳቃሽ ዕቃዎች ኮንቬንሽንና የአውሮፕላን ዕቃዎች ፕሮቶኮል ጸድቀዋል።

### *PROCLAMATION NO. 371/2003*
### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONVENTION ON INTERNATIONAL INTERESTS IN MOBILE EQUIPMENT AND THE PROTOCOL TO THE CONVENTION ON MATTERS SPECIFIC TO AIRCRAFT EQUIPMENT*

WHEREAS,the Convention on International Interests in Mobile Equipment and Protocol to the Convention on Matters Specific to Aircraft Equipment was singed in Capte Town, South Africa on 16th November 2001;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Convention and the Protocol at its session held on the 14th day of October, 2003;

*NOW, THEREFORE, in accordance with Aricle 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as "The Convention on International Interests in Mobile Equipment and the Protocol to the Convention on Matters specific to Aircraft Equipment Ratification Proclamation No. 371/2003."

2. *Ratification of the Convention and the Protocol*

The Convention on international Interest in Mobil Equipment and the Protocol to the convention on matters specific to Aircraft Equipment signed in Cape Town, South Africa on November 16th, 2001 are hereby ratified.

፫· ማስታወቂያዎች

ኢትዮጵያ ከዚህ ጋር የተያያዙትን ለተወሰኑ የኮንቬንሽንና የፕሮቶኮሉ ደንጋጌዎች ማስታወቂያ ሰጥታለች።

፬· የመሠረተ ልማት ሚኒስትር ሥልጣን

የመሠረተ ልማት ሚኒስትር ኮንቬንሽኑና ፕሮቶኮሉ በሥራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፭· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፮

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

3. *Declarations*

Ethiopia hereby makes declarations relating to certain provisions of the Convention and the Protocol, as attached herewith.

4. *Power of the Minister of Infrastructure*

The Minister of Infrastructure is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Convention and the Protocol.

5. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 14th day of October, 2003.

Done at Addis Ababa, this 14th day of October, 2003.

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA